www.ethiopianorthodox.org

# ወጣቶችና ቤተ ክርስቲያን

ክፍል አንድ

## የወጣቶችና የቤተ ክርስቲያን ትርጓሜ

በትርጓሜ ቤት ዘይቤ ቤተ ክርስቲያን የአራት ጾታ ምእመናን ስብስብ (ጉባኤ) ናት። ከዚህ ስብስብ አንዱ ዓቢይ ክፍልም «ውሉድ» ናቸው። «ውሉድ» የሚለው ቃል የሕፃናትን፣ ወጣቶችንና ጎልማሶችን ክፍል የሚያጠቃልል ግዙፍ ቃል ነው።

«ጾታ» የሚለው ቃል በዚህ አገላለጽ «ክፍል» ማለት ሲሆን በዚህ አጋጣሚ ስለ ጾታ ምእመናን ዝርዝር ከዚህ ቀጥሎ በአጭር መግለጥ ይቻላል።

### የምእመናን ስብስብ (ጉባኤ)

ሀ. በተፈጥሮ ጾታ ሲከፈል – ዕድ ወአንስት (ሴትና ወንድ)

ለ. በእድሜ ጾታ ሲከፈል – አዕሩግ ወሕፃናት/ወደቂቅ (አባቶችና ልጆች)

ሐ. በመዓርግ ጾታ – ካህናት ወመኃይምናን (ካህናትና መኃይምናን/ካህንና ጨዋ)

– ዓበ ዩ ወንኡስ (አሳዳሪና ተዳዳሪ) በሚል መድበለ ማኅበር ይከፈላል።

የቤተ ክርስቲያን ወይም የምእመናን ስብስብ ወይም «መድበለ ማኅበር» በዚህ ዓይነት ጾታ ክፍል የተከፈለ ቢሆንም በዚህ ርእሰ ትምህርት ለመናገር የተፈለገው «ውሉድ» የሚለውን ክፍል በማስመልከት ነው።

ወጣቶች የቤተ ክርስቲያን ሕዋስ ወይም አካል መሆናቸውን መገንዘብ ከተቻለ ዘንድ «ወጣቶች» ማለት ቤተ ክርስቲያን፤ ቤተ ክርስቲያን ማለትም «ወጣቶች» ማለት ጭምር መሆኑን መገንዘብ አስቸጋሪ አይሆንም።

ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተችው የሲኦል ኃይሎች ሊያናውጡት በማይችሉ መሠረት ላይ እንደሆነ ተጽፏል ማቴ. ፲፮፥፲፰። ቤተ ክርስቲያን በሁሉም ጾታ ምእመናን አንድነት ላይ የተገነባች የእግዚ አብሔር ቤት ከሆነች ወጣቱ ራሱ ቤተ ክርስቲያን (ወይም የቤተ ክርስቲያን አካል) ስለሆነ ለሕይወቱ ግምባታ የማይናወጥ ጽኑዕ መሠረት ያስፈልገዋል፤ ያም መሠረት በተግባር ሊታይ የሚችል ክርስቲያናዊ ሕይወት ነው።



በሌላም ቋንቋ ቤተ ክርስቲያንን ጠንካራና ጤነኛ የሆነ ሙሉ አካል ያላት የክርስቶስ አገልጋይ ለማድረግ የወጣቱን ትውልድ ክርስቲያናዊ ሕይወት ደኅንነት መጠበቅ ግዴታ ይሆናል። ይህ ሕይወት በአስተማማኝ ሁኔታ ሊጠበቅ የሚችለውም ወጣቱ ትውልድ ከልጅነት ጊዜው ጀምሮ በሰውና በእግዚአብሔር መካከል በጥበብና በሞገስ እንዲያድግ ማድረግ ሲቻል ነው።

ክፍል ሁለተ

## የወጣቶችና የቤተክርስቲያን ትርጓሜ

### የወጣትነት ጊዜ ወርቃማነት

«ወጣቶችና ቤተ ክርስቲያን» የሚለውን አንቀጸ ትምህርት በዚህ በማጠቃለል «ክርስ ቲያናዊ ሕይወት በወጣትነት» የሚለውን ክፍል ለመቃኘት ሲሞከር ደግሞ ክርስቲያናዊ ሕይወት በወጣትነት ዘመን የሚያስገኘውን መንፈሳዊና ማኅበራዊ በረከት በዝርዝር መመልከት ይቻላል።

ቅዱስ መጽሐፍ ስለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የልጅነት ዘመን ሲተርክ «በጥበብና በቁመት፣ በሞገስም በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ያድግ ነበር» ይላል ሉቃ.፪፥፶፪። እኛን ለማዳን ሰው የሆነው አምላክ ሕጻንም፣ ወጣትም ሆኖ ቀስ በቀስ በማደግ የልጅነት ዘመኑን በዚህ ዓይነት ሕይወት ያሳለፈው ለራሱ ክብርና ሞገስ ለማግኘት አይደለም፤ ትምህርትና አብነት ለሚያስፈልጋቸው ለዚህ ዓለም ሕፃናትና ወጣቶች ራሱን መልካም አርአያና ምሳሌ አድርጎ በማቅረብ የሕፃንነትና ወጣትነት ዘመን መንፈሳዊና ማኅበራዊ ሕይወት ምን መምሰል እንዳለበት ለማስተማር እንጂ በእርግጥ የራሱን ግዴታ ለመፈጸም አይደለም። የዓለም መድኃኒት ራሱ የዓለም መምህር ሆኖ የሰውን ልጅ ያስተማረው በቃል ብቻ ሳይሆን በተግባርም ማለት በመልካም አርአያና ምሳሌነትም ጭምር መሆኑን ለሚያውቅ አማኒ ይህን ምሥጢርም ማወቅ የሚሳነው አይሆንም። የሰው ልጅ ራሱ «ጊዜ ወርቅ ነው» እንደሚለው በእርግጥ ጊዜ ወርቅ ከሆነ የወጣትነት ጊዜን በሰውና በእግዚአብሔር ፊት የበለጠ ወርቃማ ማድረግ የሚቻለውም ይህ ሲሆን ነው – ማለት በሰውና በእግዚአብሔር መካከል በጥበብና በሞገስ ለማደግና በክርስቲያናዊ ሕይወት በተባረከ የወጣትነት ዘመን ለመኖር ሲቻል።

የልጅነትና የወጣትነት ዘመን የነፋስና የእሳት ዘመን ነው። ስለሆነም በቀዳማዊው የልጅነት ዘመን እንደነፋስ በዘፈቀደ መንፈስና በዳኃራዊው ደግሞ እንደ እሳት መተኮስና መፋጀት ምንጊዜም የነበረ፣ ያለና የሚኖር የተፈጥሮ ባሕርይ ነው። ይሕውም የልጅነትና የወጣትነት ዘመን ተፈጥሮው ከእሳትና ከነፋስ የሆነው የሰው ልጅ ይህን የተፈጥሮ ባሕርይ በተግባር የሚያሳይበት አፍላ ወቅት በመሆኑ ነው።

በውኃነትና በመሬትነት ባሕርይ የሚገኙ አንዳንድ አበው በዚህ የነፋስነትና የእሳትነት ባሕርይ ዘመን ላይ የሚገኙ ውሉድ እንደ እነሱ የሰከነ ጠባይ ማሳየት እንደአለባቸው ስለሚጠብቁ በየትኛውም ጊዜና በታ [illegible] ታዳጊ ሕፃናትና ወጣቶችን ሲተቹና ሲራገሙ፣ አልፈው ተርፈውም ዘመኑን ሲያማርሩ ይሰማሉ። ለልጅነትና ወጣትነት ባሕርይ ነፋስነትና እሳትነት ዕውቅና መስጠት ይሳናቸዋል። በዚያም ጠባያቸው ልጆች እግዚአብሔርን የሚያስቆጡ እየመሰላቸው ይጨነቃሉ።

አንድ ጊዜ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ደቀመዛሙርት ልጆቻቸውን ይባርክላቸው ዘንድ ወደጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይዘው ለመቅረብ የሞከሩትን ወላጆች የከለከሉት ልጆቹ እንዳያውኩት በማሰብ እንደሆነ ይታመናል። ማቴ.፲፱:፲፫–፲፭። ሙከራው የተደረገው ልጆች አዋኪዎች እንደሆኑ በማሰብ ቢሆንም አስተሳሰቡ ሰው ሰውኛ በመሆኑ በክርስቶስ አልተደገፈም፣ ልጆቹ ወደ ክርስቶስ እንዳይቀርቡ የሞከሩት ደቀ መዛሙርት ተገስጸዋል። የተከለከሉትም ልጆች ቀርበው በአንብሮተ እድ ተባርከዋል።

በመሠረቱ ሰውን የፈጠረ አምላክ ልጅም ይሁን ሽማግሌ ስለፍጥረቱ ምንነት ያውቃል፤ «ሕፃናትን አትከልክሉአቸው ወደእኔ ይምጡ» ያለውም ከልጅነት ባሕርይ ውጭ ሁነው ወደ እሱ እንዲቀርቡ አይደለም፤ ወጣቶችም እንዲሁ። ስለሆነም ልጆችና ወጣቶች ወደ እግዚአብሔር እንዲቀርቡ



2nd yea, Number 2, Meskerem 1992

www.ethiopianorthodox.org

የሚፈለገው የተባረከ ልጅ፣ የተባረከ ወጣት ሁነው እንዲያድጉ፣ ልቅና ስድ – አደግ በመሆን ፈንታ ከላይ እንደ ተገለጸው በሰውና በእግዚአብሔር መካከል በጥበብና በሞገስ በማደግ በመንፈሳዊውም ሆነ በማኅበራዊው ሕይወት ለመልካም ጉልምስናና ሽምግልና ኑሮ ጽኑዕ መሠረት ለመጣል እንዲበቁ፤ በዚህ ዓይነት ክርስቲያናዊ ሕይወት የነፋስና እሳት ባሕርያቸውን በማርገብና በማቀዝቀዝ የልጅነትና ወጣትነት ኑሮዋቸውን ሕይወትነት ያለው ለማድረግ እንዲችሉ በተግሣጽ በትምህርትና ምክር ለማገዝ እንጂ የእድሜያቸው ሰው እንዳይሆኑ ለማድረግ አይደለም። ወይም በአንድ ጊዜ ተወልደውና በአንድ ጊዜ አድገው የአባቶቻቸው ዘመን ሰው እንዲሆኑ ለማድረግም አይደለም። «ክርስቲያናዊ ሕይወት በወጣትነት» የሚለው ምኞት ሙሉ በሙሉ ተፈጻሚ ሊሆን የሚችለውም ልጆችና ወጣቶች በዚህ ሁኔታ የራሳቸው ዕድሜ የሚጠይቀውን ክርስቲያናዊ ሕይወት በመኖር መልካም አዳጊ ክርስቲያን ለመሆን ሲበቁ ነው።

## ክፍል ሦስት

# ከክርስቲያን ወጣቶች የሚጠበቅ የከዊንና ገቢር ግዴታ

ስለዚህ ርእስ ለመናገር በቅድሚያ የሁሉም ጾታ ምእመናን ሕይወት መመሪያ የሆነውን ቅዱስ መጽሐፍ ማናገር ግዴታ ይሆናል።

«አንተ ጎበዝ በጉብዝናህ ደስ ይበልህ፤ በጉብዝናህም ወራት ልብህን ደስ ይበለው፤ በልብህ መንገድ፣ ዓይኖችህም በሚያዩት ሂድ፤ ዳሩ ግን ስለዚህ ነገር ሁሉ እግዚአብሔር ወደ ፍርድ እንደሚጠራህ ዕወቅ...» መክ.፲፩:፱–፲።

«የጭንቀት ቀን ሳይመጣ፣ ደስ አያሰኙም የምትላቸውም ዓመታት ሳይደርሱ በጉብዝናህ ወራት...ፈጣሪህን አስብ» መክ.፲፪:፩–፰።

«አቤቱ ጌታዬ ሆይ ከልጅነቴ ጀምሮ ተስፋዬና መታመኛዬም አድርጌሃለሁ።» መዝ.፸:፭–፮።

«ፈጣሪዬ ከልጅነቴ ጀምሮ ይቅር ብልኸኛል (አስተምረኸኛል) ጌትነትህን እናገራለሁ፣ ፈጽሜ እስከ አረጅ ድረስም» መዝ.፸፩:፲፯።

«ጎልማሳውም አለው ይህን ሁሉ ከልጅነቴ ጀምሮ ጠብቄያለሁ፤ እንግዲህ ምን ቀረኝ?» ማቴ.፲፱:፳።

«ጎልማሶች ሆይ! ብርቱዎች ናችሁና፣ የእግዚአብሔር ቃል በእናንተ ዘንድ አለና፣ ክፉውንም አሸንፋችኋልና እጽፍላችኋለሁ» ፩ዮሐ.፪፥፲፬።

ስለወጣቶች መንፈሳዊ ሕይወት ትውፊት ከቅዱስ መጽሐፍ ብዙ መጥቀስ ይቻላል። ሆኖም የተጠቀሰው ቃል ሌላውን ሁሉ ስለሚወክል ለጊዜው ይበቃል። ከእያንዳንዱ ጥቅስ መረዳት እንደሚቻለው፤

ጠቢቡ ሰሎሞን በጉብዝና ወራት የሚሠራ ሥራ ሁሉ ትክክለኛ ካልሆነ በእግዚአብሔር ዘንድ እንደሚያስጠይቅ በማስጠንቀቅ በወጣትነት ወራት ራስን ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔርንም ደስ የሚያሰኝ ኑሮ መኖር በመጀመሪያው ዘመን ጀምሮ ተግባራዊ መሆን ያለበት የሰው ልጅ ግዴታ እንደሆነ ይመክራል።

ነቢዩ ዳዊት እግዚአብሔርን ተስፋ በማድረግ ማለት በእሱ በመታመንና ጌትነቱንም በመመስከር የአምልኮትን ግዴታ መፈጸም በልጅነት ዘመን መጀመር ያለበት ግዴታ መሆኑን በራሱ ምሳሌነት ይናገራል (ተናግሯል)።

ሐዋርያው ዮሐንስ ልቡናቸው ለቃለ እግዚአብሔር ዘር መልካም ምድር ለሆነውና ክፉውንም ሁሉ በማሸነፍ ኃያልነታቸውን በተግባር ለአረጋገጡት የዘመኑ ክርስቲያን ወጣቶች የጻፈው የምስጋና ቃል በተመሳሳይ ሕይወት ለተገኙና ለሚገኙ የየትኛውም ዘመን ወጣቶች ሁሉ የተደረገ ሙገሳ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል።

ከልጅነት ጀምሮ አምላካዊ ሕግንና ትእዛዝን ጠባቂ ሆኖ መኖሩን በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፊት በኩራት የተናገረው ጎልማሳ በአነጋገሩና በአስተሳሰቡ ተመካ ሂናውዳሴ – ከንቱ ወዳድ ወይም አፍቃሪ ሆኖ ባይገኝ ኑሮ «ይህን ሁሉ ከልጅነቴ ጀምሮ ጠብቄያለሁ፤ ሌላ ምን ቀረኝ?» ሲል ያቀረበው ጥያቄ ይበል የሚያሰኝ የመልካም ወጣትነትና ጎልማሳነት ቃል ነበር። ይህም ሆኖ ከዚህ ጎልማሳ የሕይወት ታሪክ ወጣቶች የሚያገኙት ትምህርት አለ፤ ከልጅነት ጀምሮ አምላካዊ ሕግንና ትእዛዝን ጠባቂ ሆኖ ማደግ የነበረና የሚኖር ሃይማኖታዊ ግዴታ መሆኑን ከዚህ ወጣት የሕይወት ታሪክ ለማወቅ መቻል አንድ ትምህርት ሲሆን በእግዚአብሔር ፊት ትንሣሒ እንጂ ተመካሂ ወጣት ሆኖ መገኘት ደካማነትና ፍሬ ቢስነት መሆኑን ማወቅ ደግሞ ሌላ ትምህርትነት አለው።

በመሆኑም ይህን ጠቅላላ ዕውቀት ማወቅና ይህን ጥንቃቄ መጠንቀቅ በዘመነ አሪትም ሆነ በዘመነ ወንጌል ከልጅነት ጊዜ ጀምሮ የሚጠበቅ ግዴታ መሆኑ በየዘመኑ ለሚነሡ አበውና ውሉድ ሁሉ ግልጽ ሊሆን ይገባል። አባቶች ወጣቱን በትምህርት ሳይወልዱና ልጆችም ከአባቶቻቸው በግብር ሳይወለዱ በመንፈሳዊው ሕይወት አባትና ልጅ ተብለው ሊጠሩ አይችሉም። ይህ ሊሆን የሚችለው አባቶች የሥጋ ልጆቻቸውን በመንፈስም መውለድ ሲችሉና ልጆችም በዚያ ዓይነት መንፈስ ተወልደው የአባቶቻቸው ልጆች ለመሆን ሲበቁ ነው።

ይስሐቅ በሥጋ ብቻ ሳይሆን በመንፈስም የአባቱና የእናቱ ልጅ የሆነ ወጣት ስለሆነ እንደ እናቱና አባቱ በእግዚአብሔር ዘንድ የተወ ደደና የተከበረ ሰው ሆኖ ኑሯል፤ የተባረከ ዘር ለማግኘትና የሕዝበ እግዚአብሔር አባት ለመሆን የበቃውም በሥጋ ብቻ ሳይሆን በመንፈስም የአብርሃምና ሣራ ልጅ በመሆኑ ነው።

ኢትዮጵያ የአያሌ ቅዱሳን አበው ሀገ ናት፤ ሌላው ቀርቶ ዘውድ ጥለው የመነኑና በዘውድ ሥልጣን ላይ ሁነውም የምናኔ ዓይነት ኑሮ የኖሩ መሪዎች የተገኙባት የቅዱሳን አበው መገኛ የሆነች ቅድስት ምድር ናት። አሁንም ቢሆን በእምነታቸው ጽናትና በትሩፋታቸው ብዛት የክርስትናው ዓለም የሚያደንቃቸው ምእመናን በብዛት የሚገኙት በዚህች ሀገር ነው። በመሆኑም ይስሐቅ በሃይማኖት አብርሃምንና ሣራን ለመተካት የቻለ አምሳያ ልጅ ለመሆን እንደበቃ ሁሉ እንዲሁ የኢትዮጵያ ቅዱሳን አበውን የሚተካ አምሳያ ልጅ በብዛት እንዲወለድ ከዚህ ዘመን ትውልድ ይጠበቃል። ወፍ ዘራሽ ሳይሆን የእነዚያ ቅዱሳን አበው ዘር እንዲረባ ይፈለጋል።

«ከዊንና ገቢር» የሚለው ቃል ወጣቱ በወጣትነት ዘመኑ ምን መሆንና ማድረግ እንዳለበት ለማመልከት የገባ ቃል ከሆነ ዘንድ በወጣትነት ዘመን የክርስቲያናዊ ሕይወት ከበርቴ መሆን የሚቻለው እንዲህ መሆንና እንዲህ ማድረግ ሲቻል ነው።

www.ethiopianorthodox.org

## ክፍል አራት

# ወጣቱን በሚመለከት ከሃይማኖት አባቶች የሚጠበቅ የከዊንና ገቢር ግዴታ

ጥቅስ፣ «እሱም ሕዝብን በሚገባ መንገድ ለእግዚአብሔር ለማዘጋጀት፤ የአባቶችን ልብ ወደ ልጆች፣ የማይታዘዙትንም ወደ ጻድቃን አእምሮ (እግዚአብሔርን ወደ ማወቅ) ለመመለስ በኤልያስ መንፈስና ኃይል ይመጣል» ሉቃ.፩:፲፯–፲፰፣ ሚል.፫:፲፬።

ይህ ቃል ለዮሐንስ መጥመቅ የተነገረና የተፈጸመ ትንቢት እንደሆነ ከዚህ ቅዱስ መጽሐፍ ሙሉ ቃል መረዳት ይቻላል። ኤልያስ ለአምልኮቱ ቀናዒ፣ በመስተጋድልነቱ በቋዒ፣ በዚህ ዓለም ኑሮው ባሕታዊና መልአካዊ፣ በጸሎቱ ሥሙርነት ፍጹም የእግዚአብሔር ሰው መሆኑን ያረጋገጠ መንፈሳዊ አባት መሆኑ ይታወቃል። ፩ነገ.፲፯:፩–፯፣ ፲፰:፩–፵፯፣ ፲፱:፩–፳፩፣ ያዕ.፭:፲፯።

መጥመቁ ዮሐንስም በኤልያስ መንፈስና ኃይል የተነሣ ካህን፣ ነቢይና ሰማዕት ሆኖ መነሣቱ የአባቶችን ልብ ወደ ልጆች ለመመለስ ብቃት ያለው አባት (መምህር) ለዚህ ዓለም እጅግ በጣም አስፈላጊ እንደ ሆነ የሚያመለክት ነው። በትክክለኛ እምነትና ምግባር ጸንተው አምልኮተ እግዚአብሔርን ሲፈጽሙ የኖሩ አበውን ልብ ወደ ውሉድ እንዲተላለፍ የማድረጉ ተግባር ከምንም ነገር የሚበልጥ ኃላፊነት በመሆኑ ይህን ኃላፊነት በተግባር መወጣት ከሃይማኖት አባቶች ብቻ ሳይሆን ከወላጆችና ከኅብረተሰቡ ሕያዋን አበውም የሚጠበቅ ግዴታ መሆን ይኖርበታል። ይህ ካልሆነማ ተተኪው ትውልድ አሳዳጊ የበደለው ልቅና – ስድ አደግ ይሆንና የአገርንና የቤተ ክርስቲያንን አደራ ለመቀበል ብቃት የጎደለው መሆኑ አይቀሬ ይሆናል።

የአባቶችን ልብ ወደ ልጆች የመመለሱ ተግባር አፈጻጸም የሁሉም ግዴታ ሊሆን የሚችለው ወላጆች የአብርሃምና የሣራ ዓይነት እናትና አባት ከሆኑ ብቻ ነው። ያለዚያ ግን እንደ ኤሳው ያለውን አባት ልብ ወደ ልጆች እንዲመለስ ማድረግ ተተኪውን ትውልድ መበከል ስለሚሆን አለማድረጉ በኃላፊነት የሚያስጠይቅ አይሆንም።

ኢትዮጵያ ለሃይማኖታቸው ቀናዕያን የሆኑ አበውና ውሉድ ሲፈራረቁባት የኖሩ ሀገረ እግዚአብሔር ናት። በሃየማኖት ትምህርት የሀገር ነፃነትና አንድነት፣ የሰላምና ብልጽግና አስፈላጊነት የታወቀባት መጽሐፍ ቅዱሳዊት ሀገር ናት። በሕዝቧ የፈጠራ ችሎታ የአያሌ አስደናቂ ቅርሳ ቅርስ ባለቤት ለመሆን የበቃች የታሪክ ሀገር ናት። ጥንታውያን ገዳማት የሚገኙባትና አያሌ የቃል ኪዳን ቅዱሳን የተነሡባት መንፈሳዊት ሀገር ናት።

ይህ ሁሉ የሆነው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ህልውናና የተዋጣ ትምህርት ስለሆነ የኢትዮጵያ ሕዝበ ክርስቲያን በዚህ ኢትዮጵያዊነቱ ጸንቶ ይኖር ዘንድ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንም በተዋሕዶ እምነቷና ትምህርቷ ለዘላለም ጸንታ መኖር ይኖርባታል።

## ክፍል አምስት

# የወጣቶች ኦርቶዶክሳዊ ግዴታ

፩. ኦርቶዶክሳዊ እምነትና ምግባር በአገርና ቤተ ክርስቲያን ፍቅር፣ በኢትዮጵያዊ ጨዋነትና ቁም – ነገረኝነት፣ በሰው አከባሪነትና መንፈሳዊ ጀግንነት የአባቶችና እናቶች አምሳያ ልጅ ሆኖ መገኘት፣

፪. ሲነግሩትና ሲመክሩት የሚሰማ፣ ሲመሩት የሚከተል፣ ከፉና ደግን ከስሕተት ሳይሆን ከአበው ምክርና ከቃለ እግዚአብሔር የሚማር፣ ተው ሲሉት በቀላሉ የሚመለስ ሰው አከባሪና እግዚአብሔርን ፈሪ ሆኖ መገኘት፣

፫. ሃይማኖቱንና የቤተ ክርስቲያን አባልነቱን እየቀያየረ እንደ ኤሳው ብኩርናውን/ክብሩን ለምሥር የሚሸጥ አሳፋሪ ልጅ አለመሆን፣

፬. ከጋብቻና ከድንግልናዊ ሕይወት ውጭ የሆነ ሌላ የክርስትና ሕይወት ስለሌለ የሁሉም ዓይነት ችግር መጋለጫ የሆነውን ሦስተኛውን ዓይነት ኑሮ ላለመኖር መጠንቀቅ ወይም ከዚያ ኑሮ ፈጥኖ መውጣት፣

፭. የአባቶችንና እናቶችን ኦርቶዶክሳዊ እምነትና አምልኮ በልማድ ሳይሆን በትምህርታዊ ዕውቀት በመውረስ መፈጸም፣

፮. በኦርቶዶክሳዊ ቋንቋ በመጸለይና በኦርቶዶክሳዊ ዜማ በመዘመር፣ ቅዱስ መጽሐፍን በኦርቶዶክሳዊ ቋንቋ በማንበብና በመተርጎም፣ በመማርና በማስተማር ወዘተ…አምልኮተ እግዚአብሔርን ከልጅነት ጀምሮ መፈጸም ማለት በዚህ ዓይነት ኦርቶዶክሳዊ እምነትና ምግባር በሰውና በእግዚአብሔር መካከል በጥበብና በሞገስ ማደግ፣ መኀልመስ «የወይፈን በሬ» መሆን ማለት እንደ ሕፃን ሳይሆን እንደ ባለ አእምሮ የሚያስብ የልጅ ሽማግሌ ለመሆን መብቃት፣

፯. በዚህ ዓይነት ሕይወት ሥጋዊና ዓለማዊ የሆነውን የወጣትነት ሰውነት መንፈሳዊና ሰማያዊ ማድረግ ወዘተ… ከኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ወጣቶች የሚጠበቅ ኦርቶዶክሳዊ ግዴታ ሊሆን ይገባል።

ወጣቱ ትውልድ የእግዚአብሔር መንፈስ ማለት የጥበብና የማስተዋል መንፈስ፣ የምክርና የኃይል መንፈስ፣ የዕውቀትና እግዚአብሔርን የመፍራት መንፈስ ማረፊያ ከሆነ ኢሳ.፲፩፥፪ የወጣትነት ዘመን የክርስቲያናዊ ሕይወት ፍሬ የሚለቀምበት የበረከት ዘመን ሲሆን ማየት እንደ ተአምር የሚቆጠር አይሆንም።

በአሁኑ ጊዜ ይህ ዓይነቱ ሕይወት በብዙዎች ኦርቶዶክሳውያን ወጣቶች ላይ በግልጽ በመታየት ላይ ስለሆነ ቤተ ክርስቲያናችን ይህን ጸጋ ምልዓት የላጡ ለማድረግ አቀባበሏን ማሳመር ይኖርባታል። የራቀውን በማቅረብና የመጣውንም በደስታ በመቀበል በመልካም አያያዝ የመጋቢነት ተግባሯን መፈጸም ይገባታል። በየአጥቢያው የሰንበት ት/ቤት በማቋቋምና በማስተማር ወጣቱ ትውልድ በጥምቀት ብቻ ሳይሆን በዕውቀትም ተወልዶ በዐራቱም ማዕዘኑ ኦርቶዶክሳዊ እንዲሆን ማድረግ ለሚያስችል ሐዋርያነትና ሐዋርያዊ ተግባር አፈጻጸም ከምንጊዜውም በበለጠ ዝግጁ መሆን ይጠበቅበታል። የወጣቱ ትውልድ እምነት እንደ ለማኝ ጥሬ ድብል ቅልቁ የወጣ መሆን የለበትም። ከስንፍና ሁሉ የሚከፋ ስንፍና፣ ከድክመት ሁሉ የሚከፋ ድክመት ይሆናል። ይህ ዓይነቱ መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ለቤተ ክርስቲያናችን ጥንካሬ ተጨማሪ ምልክት ስለሆነ የሚያኮራ ነው። ስለሆነም ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል።

የአብ ጸጋ የወልድ ቸርነት፣ የመንፈስ ቅዱስ አንድነት ከቤተ ክርስቲያናችን ወጣቶች ጋር ይሁን ዛሬም፣ ዘወትርም ለዘለዓለሙ አሜን፤ ❖

መልዓከ ታቦር ተሾመ ዘሪሁን